የኢትዮጵያ
ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)

# 154ኛ ልዩ መግለጫ

# በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ አርሲ ዞን ሸርካ ወረዳ እና ቄለም ወለጋ ዞን ጊዳሚ ወረዳ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

ታህሳስ 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## ማውጫ

የኢትዮጵያ አስተዳደራዊ ካርታ........................................................................................................1

1. የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ........................................................................................................2

2. መግቢያ፡........................................................................................................3

3. የምርመራ ስራው የተደረገበት ጊዜ እና በምርመራ ስራው የተሸፈኑ አካባቢዎች፡........................................3

4. አላማ፡........................................................................................................3

5. የምርመራ ስራው እና ውስንነቶች እና ያጋጠሙ ችግሮች፡........................................................................4

6. የምርመራ ስራው ስነ ዘዴ፡........................................................................................................4

7. የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ዝርዝር ሁኔታ፡........................................................................................4

7.1. ግድያ፡........................................................................................................5

7.2. የአካል ጉዳት፡........................................................................................................7

7.3. ንብረት ውድመት፡........................................................................................................8

8. በተፈጸመው ጥቃት የተገደሉ ሰዎች ምስል፡........................................................................................8

9. እገታ፡........................................................................................................10

10. በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፡.................................10

ተያያዥ የህግ ግዴታዎች፡........................................................................................................11

የኢሰመጉ ጥሪ፡........................................................................................................12

ዋና ጽ/ቤት፡ አዲስአበባ

አ.አ ስታዲየም አጠገብ፣ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ሣኅለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ቢሮ ቁጥር 19

ኢ-ሜይል:info@ehrco.org

ድረገጽ: www.ehrco.org

ፌስቡክ፡https://www.facebook.com/ehrco1/

ትዊተር፡ https://www.twitter.com/ehrcoethio

ቴሌግራም፡ https://t.me/ehrco

የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ፡ አዲስ አበባ

ስልክ: (+251) 011 558-2387

ኢሜይል:info@ehrco.org

ቀጠና / ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ሐዋሳ - ስ.ቁ (+251) 046 220-4500፣ ፖ.ሳ.ቁ 360

አርባምንጭ - ስ.ቁ (+251) 046 18 18 344


ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና፡ባሕርዳር- ስ.ቁ (+251) 058 220-0240፣ ፖ.ሳ.ቁ 1115

ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና አዳማ -

ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና ሐረር - ስ.ቁ (+251) 025 411 6845፣ ፖ.ሳ.ቁ 2596

ጂግጂጋ - ስ.ቁ (+251) 025 2 78 42 40

ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና፡አዲስ አበባ- ስ.ቁ (+251)011 551-7704፣ ፖ.ሳ.ቁ




## የኢትዮጵያ አስተዳደራዊ ካርታ

(በምርመራ ስራው የተሸፈኑ ቦታዎች በካርታው ላይ ስማቸው ተገልጿል)

## 1. የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

**የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ - ኢሰመጉ** በበጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሠረት ሐገር በቀል ድርጅት ሆኖ በ 1984 ዓ.ም የተመሠረተና በምዝገባ ቁጥር 1146 ከ 02/11/11 ዓ.ም ጀምሮ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ዳግም ተመዝግቦ በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅት ነው፡፡ ኢሰመጉ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ሲሆን፣ ዓላማውም በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ ነው፡፡

ኢሰመጉ የተቋቋመበት ዋነኛ ዓላማው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የጎለበተባት፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነባት እና ሰብዓዊ መብቶች የሚከበሩባት ኢትዮጵያን ማየት ነው፡፡ በሥራውም ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የኃይማኖት ተቋም፣ የብሔረሰብ ቡድን፣ ማኅበራዊ መደብ ወዘተ የማይወግን፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ነው። ኢሰመጉ ላለፉት 30 ዓመታት በቆመላቸው ዐበይት ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ ሁለንተናዊ፣ ሐገራዊና ሕዝባዊ ተልዕኮ በመያዝ በነደፋቸው በርካታ የመርሐ -ግብር ተግባራት አማካኝነት ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የሕግ የበላይነትና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲሰፍንና በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲኖር የበኩሉን አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛል።

የኢሰመጉ ዋነኛ ተግባሩ የኢትዮጵያን የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝና ሁኔታ መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በማጣራትና በመተንተን በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው። ኢሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ የመኖር ልማድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና ተገቢው የፖሊሲና የአፈጻጸም እርማት እንዲደረግ ሲወተውትና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁይቀጥላል። ከኢሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ክትትል ተግባራት መካከል፣ የሕግ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቃቸውን መከታተል፣ የፍርድ ቤቶችን ሒደት ፍትሓዊነት መከታተል እንዲሁም በመንግሥት የወጡና የሚወጡ ሕጎችን ይዘትና አፈጻጸማቸውን ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር መመርመር ይገኙበታል። ከእነዚህ በተጓዳኝ ኢሰመጉ በተለይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ሰዎች የተለያየ ደረጃና መልክ ያለው የሕግ ድጋፍ ይሰጣል።

በእስካሁኑ ቆይታው ኢሰመጉ 39 መደበኛ መግለጫዎችና 153 ልዩ መግለጫዎችን በተጨማሪም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል። ኢሰመጉ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ቢሆን፣ ሁኔታና ዐቅም በፈቀደለት መጠን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነት እና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ በመሥራት ላይ ይገኛል።

## 2. መግቢያ፡

በታጣቂ ቡድኖች የሚፈጸሙ ጥቃቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ መጠናቸውን በመጨመር እየቀጠሉ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ጥቃቶች በአንዳንድ አካባቢዎች በተደጋጋሚ ጊዜ የሚፈጸሙ ቢሆንም ከመንግስት በኩል ተገቢው በቂ ትኩረት ባለመሰጠቱና ዘላቂ መፍትሔ ባለመበጀቱ ምክንያት እንደቀጠሉ ይገኛሉ፡፡ የኦሮሚያ ክልል በታጣቂዎች ተደጋጋሚ ጥቃት ከሚፈጸምባቸው ክልሎች አንዱ ሲሆን ይህም ጥቃት በዋናነት ማንነትን መሰረት ያደረገ ጥቃት ነው፡፡ ይህም ጥቃት በሰዎች ላይ ግድያን፣ የአካል ጉዳትን፣ ንብረት ውድመትን፣ መፈናቀልን እንዲሁም ሌሎች መጠነ ሰፊ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን እያስከተለ ይገኛል፡፡ የሚደርሱ ጥቃቶች ዘላቂ መፍትሔ ባለማግኘታቸውና መንግስተ የነዋሪውን ደህንነት በተገቢው ሁኔታ ማስጠበቅና ሰብዓዊ መብቶቻቸውን ማስከበር ባለመቻሉ ምክንያት በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ነዋሪዎች ከፍተኛ ለሆነ ችግር እየተዳረጉ ይገኛሉ፡፡

## 3. የምርመራ ስራው የተደረገበት ጊዜ እና በምርመራ ስራው የተሸፈኑ አካባቢዎች፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) ከህዳር 28 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 02 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ጢጆ ለቡ ቀበሌ፣ ሐላ ጢጆ ሴሮ ቀበሌ እና በሮቤ እንደቶ ቀበሌዎች ባለሙያዎችን በማሰማራት በተጠቀሱት አካባቢዎች ላይ ህዳር 14 ቀን፣ ህዳር 21 እና ህዳር 24 ቀን 2016 ዓ.ም የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የምርመራ ስራን አከናውኗል፡፡

በተጨማሪም በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን ጊዳሜ ወረዳ ማልኢኩ መንደር ህዳር 14 ቀን 2016 ዓ.ም በታጣቂዎች በተፈጸመ ጥቃት የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ሞንህም አጥቢያ በጸሎት ላይ የነበሩ የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን እና ምዕመናን መገደላቸውን ኢሰመጉ መረጃዎች የደረሱት ቢሆንም የአካባቢው የጸጥታ ሁኔታ ምቹ ባለመሆኑ ምክንያት ያልተከናወነ ቢሆንም ኢሰመጉ ለኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ዋና ጽ/ቤት በተጠቀሰው አካባቢ በአባላት ላይ የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ እንዲያጋሩን በደብዳቤ ቁጥር ER3-N35-112-23 በቀን 11/04/2016 ዓ.ም ተጠይቋል፡፡

## 4. አላማ፡

የእዚህ መግለጫ አላማ በኦሮሚያ ክልል የተለያያ አካባቢዎች በታጣቂ ቡድኖች በተደጋጋሚ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዲቆሙ ማሳሰብ ሲሆን ከእዚህ በተጨማሪ ጥሰት ፈጻሚዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ ጥሰት ለተፈጸመባቸው ሰዎች ደግሞ ተገቢ የሆነ ካሳ እና ፍትህ እንዲያገኙ እንዲሁም በክልሉ ላሉ ነዋሪዎች የክልሉ እና የፌደራል መንግስት በቅንጅት በመሆን ተገቢውን ጥበቃ እንደያደርጉ ማሳሰብ እና የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ሰንዶ መያዝ ይገኙበታል፡፡

ኢሰመጉ የዚህን ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ዘገባ ይዘትና ዓላማ በተፃረረ መልኩ፣ ከሕግና ከመልካም አስተሳሰብ ውጪ በሆነ መንገድ ማንም እንዲጠቀምበት አይፈቅድም። ይህንንም ዘገባ የሐገር ሰላምን ለማደፍረስ፣ ግለሰቦችንም ሆነ ቡድኖችን ለማጥቃት፣ ከሕግ አግባብ ውጪ ሌሎች ሲጠቀሙበት ቢገኝ ኢሰመጉ ከወዲሁ አጥብቆ ያወግዛል፣ ኃላፊነቱንም እንደማይወስድ ያሳስባል።

## 5. የምርመራ ስራው እና ውስንነቶች እና ያጋጠሙ ችግሮች፡

የዚህ ዘገባ የምርመራ ሥራ በሚከናወንበት ወቅት ኢሰመጉ የሚከተሉት ዋና ዋና ውስንነቶች እና ተግዳሮቶች አጋጥመውታል፡-

- የምርመራ ስራው በተሰራባቸው የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች ያለው የጸጥታ ስጋት፣
- የምርመራ ስራው የተሰራበት የኦሮሚያ ክልል ምስራቅ አርሲ ዞን ፖሊስ መምሪያ መረጃ ያለማጋራት ችግር፣
- ምርመራ ስራ በተሰራበት አካባቢ ያለው የትራንስፖርት ችግር፣
- የምርመራ ስራ የተሰራበት አካባቢ ላይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸመባቸው ተጎጂዎች ካለባቸው ስጋት እና ከደረሰባቸው ጉዳት የተነሳ መረጃ ለማጋራት ፈቃደኛ ያለመሆን፣

## 6. የምርመራ ስራው ስነ ዘዴ፡

ይህ መግለጫ የተዘጋጀው ኢሰመጉ የሰብዓዊ መብት የምርመራ ባለሙያዎች ባደረጉት ቃለመጠይቆች (ከተጎጂዎች፣ ምስክሮች፣ ከቤተክርስቲያን አባቶች፣ እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ያካትታል)፣ የመስክ ምልከታ ስራዎች፣ ከሀይማኖት ተቋማት የተገኙ አስረጂ ሰነዶችን በመጠቀም መረጃዎችን ኢሰመጉ አሰባስቧል፡፡

የምርመራ ቡድኑ በተጠቀሱት አካባቢዎች ተዘዋውሮ የሟች ቤተሰቦችን፣ በጥቃቱ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን፣ የዓይን ምስክሮችን፣ የቀብር ስርዓቶችን ያከናወኑ የቤተ-ክርስትያን አባቶችን፣ የዞን ፖሊስ ኃላፊዎችንና ሌሎች የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሞ ልዩ ልዩ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን አሰባስቧል፡፡

ከእነዚህ በተጨማሪ የምርመራ ቡድኑ የጅምላ እንዲሁም የግለሰብ መቃብሮችን፣ በግጭቱ ምክንያት የወደሙ ንብረቶችን እና ሌሎች ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ቦታዎች ተዘዋውሮ በመጎብኘት መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡

## 7. የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ዝርዝር ሁኔታ፡

ኢሰመጉ ህዳር 28 ቀን 2016 ዓ.ም ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ በታጣቂ ቡድኖች ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መፈጸማቸውን የገለጸ ሲሆን ይህንንም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በአካል በአካባቢው በመገኘት ተጨማሪ የምርመራ ስራዎችን በመስራት ዝርዝር ዘገባን እንደሚያወጣ ቃል መግባቱ ይታወሳል፡፡

በመሆኑም በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ውስጥ ባሉ ሶሌ ዲገሉ፣ ጢጆ ለቡ፣ ዋጂ ኮኔ፣ ሔላ ጢጆ ሴሮ፣ ሮቤ እንደቶ ቀበሌዎች እና በአርሲ ዞን በቆጂ እና ሽርካ ወረዳ መካከል ከሚገኝ መንገድ ላይ በተለያዩ ቀኖች በታጠቁ ቡድኖች ጥቃት የተፈጸመ  መሆኑን በእዚህም ጥቃት ምክንያት 53 ሰዎች ላይ ግድያ፣ 2 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት እና በቀበሌዎቹ በርካታ ቁጥር ባላቸው መኖሪያ ቤቶች ላይ ቃጠሎ እና ዘረፋ  መፈጸሙን አረጋግጧል፡፡ የተፈጸሙትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ዝርዝር ከእዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 7.1. ግድያ፡

ኢሰመጉ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አርሲ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር አ/ሀ/ስ/682/2016 ዓ.ም በቀን 28/03/2016 ዓ.ም ባገኘው መረጃ እና ከተጎጂ ቤተሰቦች ከአይን እማኞች እና ከቤተክርስቲያን አባቶች ባገኘው መረጃ መሰረት በምስ ራቅ አርሲ ሀገረ ስብከት በሽርካ ወረዳ ሶሌ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን እንዲሁም ዲገሉ ማርያም ቤተክርስቲያን እና በሮቤ አንደቶ ደብረ ምጥማቅ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን አካባቢ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ላይ አሰቃቂ ግድያዎች መፈጸማቸውን ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ህደር 14 ቀን 2016 ዓ.ም ምሽት ሶሌ ዲገሉ በተባለ ቀበሌ ውስጥ የተደራጁ ታጣቂ ቡድኖች ወደ ቀበሌው ዘልቀው በመግባት 17 ሰዎችን በአሰቃቂ ሁኔታ የገደሉ ሲሆን በተመሳሳይ በእዚሁ ወረዳ ጢጆ ለቡ በተባለ ቀበሌ ውስጥ በተመሳሳይ ሰዓት የተደራጁ ታጣቂ ቡድኖች 11 ሰዎችን ከመኖሪያ ቤታቸው መርጠው በማውጣት በአሰቃቂ ሁኔታ ገድለዋል፡፡

በድምሩ ከላይ በተጠቀሱት ቀበሌዎች ውስጥ 28 ሰዎች የተገደሉ ሲሆን ከሟቾች ውስጥ 7 ሴት እና 21 ወንዶች ይገኙበታል፡፡ በታጣቂ ቡድኖቹ ከተገደሉት ሰዎች መካከል የ70 ዓመት አዛውንት፣ የ12 ዓመት ታዳጊ፣ የ8 ወር ህጻን እና የ28 ቀን ጨቅላ ህጻን እንዲሁም ነፍሰጡር ሴቶች የሚገኙ ሲሆን ከሟቾች መካከል አብዛኛዎች የአንድ ቤተሰብ አባላት ናቸው፡፡ በእዚህ ጥቃት የተገደሉ 17 ሰዎች በሶሌ ዲገሉ መድሐኒዓለም ቤተክርስቲያን በአንድ መቃብር፣ 11 ሰዎች በሴሮ ሚካኤል በአንድ መቃብር የቀብር ስነስርዓታቸው የተፈጸመ ሲሆን በተመሳሳይ በሽርካ ወረዳ ዋጂ ኮኔ በተባለ ቀበሌ ህዳር 18 ቀን 2016 ዓ.ም 8 ሰዎች የተገደሉ ሲሆን ሟቾችም በኮኔ እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል፡፡

ሌላው ጥቃት የተፈጸመበት ቀበሌ በእዚሁ ሽርካ ወረዳ ውስጥ የሚገኘው ሔላ ጢጆ ሴሮ ቀበሌ ሲሆን ህዳር 24 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 12 ሰዓት በታጣቂ ቡድኖች በተፈጸመ ጥቃት 5 ሰዎች በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደሉ ሲሆን የሟቾች የቀብር ስነስርዓት በጎቤሳ ደስ/ቅ/ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡ በእዚሁ ወረዳ ሮቤ እንደቶ ቀበሌ ህዳር 21 ቀን 2016 ዓ.ም ከ ሌሊቱ 8 ሰዓት አካባቢ ሶስት ሰዎች ተገድለዋል፡፡ በተጨማሪም በአርሲ ዞን በቆጂ እና ሽርካ ወረዳ መካከል ከሚገኝ መንገድ ላይ ከህዝብ ማመላለሻ መኪና ውስጥ የታጠቁ ቡድኖች 4 ሰዎችን በማስወረድ በአሰቃቂ ሁኔታ ገድለዋል፡፡

| ተ.ቁ | የተገደለው ሰው ሙሉ ስም | ዕድሜ | ጾታ | የተገደለበት ቀን | የተገደለበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አበበ ወንድምአገኝ | 77 | ወንድ | 2/01/2016 ዓ.ም | ሶሌ ነጌሌ ቀበሌ |
| 2 | አቶ ቦጋለ ወ/ጊዮርጊስ | 75 | ወንድ | | ሶሌ ነጌሌ ቀበሌ |
| 3 | መ/ር አማረ ወንድሙ | 46 | ወንድ | | ሶሌ ነጌሌ ቀበሌ |
| 4 | አቶ ጌታ አበበ | 24 | ወንድ | 11/02/2016 ዓ.ም | ጋዶ 01 |
| 5 | አቶ አምዴ መንግስቱ ኃይሌ | 70 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ጢጆ ለቡ |
| 6 | አቶ ደምሱ አርምዴ ኃ/ሚካኤል | 71 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ጢጆ ለቡ |
| 7 | ወ/ሮ አሰለፍ ጃርሶ (የሙሉ ስምንት ወር | 42 | ሴት | 14/03/2016 ዓ.ም | ጢጆ ለቡ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ነፍሰጡር) | | | | |
| 8 | አቶ በለጠ ደምሉ ገዳ | 28 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ጢጆ ለቡ |
| 9 | ወጣት አብረሃም ደምሱ አርምዴ | 16 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ጢጆ ለቡ |
| 10 | ወጣት ሰብለ ደምሱ አርምዴ | 14 | ሴት | 14/03/2016 ዓ.ም | ጢጆ ለቡ |
| 11 | ወጣት ሳሙኤል ደምሱ አርምዴ | 12 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ጢጆ ለቡ |
| 12 | ወጣት ማሙሽ አበበ | 12 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ጢጆ ለቡ |
| 13 | ወ/ሮ በላይ ደቦጭ ይፍሩ | 36 | ሴት | 14/03/2016 ዓ.ም | ጢጆ ለቡ |
| 14 | ወጣት ኪዩ ሲሳይ ደምሱ | 14 | ሴት | 14/03/2016 ዓ.ም | ጢጆ ለቡ |
| 15 | አቶ ደለለኝ አሰፋ ወ/ጻዲቅ | 65 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 16 | ህፃን ማሚቱ ደለለኝ አሰፋ | 70 ቀን | ሴት | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 17 | ወ/ሮ መሠረት ጌቱ እሼቱ | 35 | ሴት | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 18 | አቶ ስዩም በቀለ ፊቼ | 66 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 19 | አቶ አበበ ስዩም በቀለ | 40 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 20 | ወጣት ውቢቱ ስዩም በቀለ | 27 | ሴት | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 21 | ወጣት ፈቀደ ስዩም በቀለ | 18 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 22 | ታዳጊ መኩሪያ ስዩም በቀለ | 4 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 23 | አቶ አበበ ስዩም በቀለ | 40 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 24 | ወ/ሮ ፀሐይ ሲሳይ | 30 | ሴት | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 25 | ታዳጊ ዳግም አበበ ስዩም | 6 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 26 | ህፃን ሕይወት አበበ ስዩም | 3 | ሴት | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 27 | ህፃን ታምራት አበበ ስዩም | 8 ወር | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 28 | ወ/ሮ ምሪ አበበ | 36 | ሴት | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 29 | አቶ ሰለሞን ሐብቴ | 40 | ወንድ | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 30 | ወ/ሮ ጽጌ ጥጋቡ ደምሴ | 58 | ሴት | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 31 | ወ/ሮ አያሀሉሽ [h1]ተድላ | 36 | ሴት | 14/03/2016 ዓ.ም | ሶሌ ጉና |
| 32 | አቶ ማንዬ ተ/አረጋይ | 80 | ወንድ | 18/03/2016 ዓ.ም | ዋጂ ኮኔ |
| 33 | ወ/ሮ የሺ ኃይሉ | 70 | ሴት | 18/03/2016 ዓ.ም | ዋጂ ኮኔ |
| 34 | አቶ ሽመልስ ማንዬ | 35 | ወንድ | 18/03/2016 ዓ.ም | ዋጂ ኮኔ |
| 35 | አቶ ለማ ማንዬ | 30 | ወንድ | 18/03/2016 ዓ.ም | ዋጂ ኮኔ |
| 36 | ወ/ሮ ብዙነሽ ንጉሴ | 28 | ሴት | 18/03/2016 ዓ.ም | ዋጂ ኮኔ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 37 | ወጣት ሂሩት ንጉሴ | 26 | ሴት | 18/03/2016 ዓ.ም | ዋጂ ኮኔ |
| 38 | ወጣት ጌታሁን ሽመልስ | 13 | ወንድ | 18/03/2016 ዓ.ም | ዋጂ ኮኔ |
| 39 | ታዳጊ ዳኙ ሽመልስ | 8 | ወንድ | 18/03/2016 ዓ.ም | ዋጂ ኮኔ |
| 40 | ወ/ሮ አቦነሽ ገድሉ ተመኘኝ | 70 | ሴት | 24/03/2016 ዓ.ም | ሑላ ጢጆ ሴሮ |
| 41 | አቶ መለሰ ታፈሰ ወ/መስቀል | 53 | ወንድ | 24/03/2016 ዓ.ም | ሑላ ጢጆ ሴሮ |
| 42 | አቶ ፀጋዬ ጥላሁን መንገሻ | 68 | ወንድ | 24/03/2016 ዓ.ም | ሑላ ጢጆ ሴሮ |
| 43 | አቶ ንጉሴ ተክሌ መንገሻ | 35 | ወንድ | 24/03/2016 ዓ.ም | ሑላ ጢጆ ሴሮ |
| 44 | ወጣት መስፍን ተክሌ መንገሻ | 21 | ወንድ | 24/03/2016 ዓ.ም | ሑላ ጢጆ ሴሮ |
| 45 | አቶ ከዲር ሁሴን መኮ | 40 | ወንድ | 24/03/2016 ዓ.ም | ሑላ ጢጆ ሴሮ |
| 46 | አቶ ኡመኖ አብዱሮ | 39 | ወንድ | 24/03/2016 ዓ.ም | ሑላ ጢጆ ሴሮ |
| 47 | አቶ ቃኘው ይልማ | | ወንድ | | ሮቤ አንደቱ |
| 48 | አቶ ሙላቱ ስዩም | | ወንድ | | ሮቤ አንደቱ |
| 49 | አቶ ጌቱ ሙላቱ | | ወንድ | | ሮቤ አንደቱ |
| 50 | መ/ር(መሪጌታ) ናሁ ሰናይ አዳም አለማ | 35 | ወንድ | 07/04/2016 ዓ.ም | በቆጂ እና ሽልካ መካከል ጋለማ የሚባል አካባቢ ከመኪና ባመስወረድ የተገደሉ |
| 51 | ዲያቆን አበበ ፀጋዬ | 32 | ወንድ | 07/04/2016 ዓ.ም | በቆጂ እና ሽልካ መካከል ጋለማ የሚባል አካባቢ ከመኪና ባመስወረድ የተገደሉ |
| 52 | አቶ አውጉቸው በላይነህ | 30 | ወንድ | 07/04/2016 ዓ.ም | በቆጂ እና ሽልካ መካከል ጋለማ የሚባል አካባቢ ከመኪና ባመስወረድ የተገደሉ |
| 53 | አቶ ሰመረ አደፍረስ | 29 | ወንድ | 07/04/2016 ዓ.ም | በቆጂ እና ሽልካ መካከል ጋለማ የሚባል አካባቢ ከመኪና ባመስወረድ የተገደሉ |

የምርመራ ስራው ከተጠናቀቀ በኋላ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ውስጥ በታጣቂዎች የሚፈጸመው ጥቃት የቀጠለ ሲሆን ታህሰስ 15 ቀን 2016 ዓ.ም ሶሌ ዲገሉ ቀበሌ ውስጥ ሁለት ወንድማማቾች የተገደሉ ሲሆን የሟቾች አባት ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ዕድሜ | ጾታ | የሙብት ጥሰቱ የተፈጸመበት ቦታ | ቀን | የደረሰው የሙብት ጥሰት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወገኔ በቀለ ደምሴ | 18 | ወንድ | ሽርካ ወረዳ ሶሌ ዲገለ ቀበሌ | 15/4/2016 ዓ.ም | ግድያ |
| 2 | ደየን በቀለ ደምሴ | 16 | ወንድ | ሽርካ ወረዳ ሶሌ ዲገለ ቀበሌ | 15/4/2016 ዓ.ም | ግድያ |
| 3 | በቀለ ደምሴ | 45 | ወንድ | ሽርካ ወረዳ ሶሌ ዲገለ ቀበሌ | 15/4/2016 ዓ.ም | የአካል ጉዳት |

### 7.2. የአካል ጉዳት፡

በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ዋጂ ኮኔ በታጣቂ ቡድኖች በተፈጸሙ ጥቃት ምክንያት በ6 ዓመት እና በ7 ዓመት ህጻናት ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ዕድሜ | ጾታ | ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሰብለ ሽመልስ ማንዬ | 7 | ሴት | 18/03/2016 ዓ.ም |
| 2 | ቅድስት ሚሊዮን ማንዬ | 6 | ሴት | 18/03/2016 ዓ.ም |

### 7.3. ንብረት ውድመት፡

በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ የ3 ቀበሌ ነዋሪዎች አብዛኛው ቤቶች የተቃጠሉ ሲሆን ከቃጠሎ የተረፈው ንብረት ደግሞ ለዝርፊያ ተዳርጓል፡፡ በእዚህም ምክንያት ከእነዚህ ቀበሌዎች የተፈናቀሉ ሰዎች በወረዳው ሽርካ ከተማ ተበታትነው ይገኛሉ እንዲሁም ወቅቱ በማሳ ላይ ያለ እህል የሚሰበሰብበት ወቅት ቢሆንም ባለው የጸጥታ ስጋት ምክንያት አርሶ አደሩ ይህንን ማድረግ አልቻለም፡፡ በጥቃቱ ምክንያት የደረሰውን የንብረት ውድመት መጠንን የምርመራ ስራ በመስራት ለመግለጽ በአካባቢው የነበረው የጸጥታ ሁኔታ ሊፈቅድ በለመቻሉ ይህንን የደረሰውን ትክክለኛ የውድመት መጠን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

## 8. በተፈጸመው ጥቃት የተገደሉ ሰዎች ምስል፡

### 8.1. በተፈጸመው ጥቃት የተገደሉ የአንድ ቤተሰብ አባላት ምስል፡

| | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| አቶ አበበ ስዩም በቀለ | ወጣት ፍቃዱ ስዩም | ወጣት ውቢት ስዩም በቀለ |
| ዕድሜ፡ 40 | ዕድሜ፡ 18 | ዕድሜ፡ 27 |

| | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| ህጻን ህይወት አበበ ስዩም | ህጻን ዳግም አበበ ስዩም | ህጻን ታምራት አበበ ስዩም |
| ዕድሜ፡ 3 | ዕድሜ፡ 6 | ዕድሜ፡ 8 ወር |

| | | | |
|---|---|---|---|
|  |  |  |  |
| አቶ ስዩም በቀለ ፊቼ | ወ/ሮ ጽጌ ጥጋቡ ደምሴ | ወ/ሮ ምሪ አበበ | ወ/ሮ ጸሀይ ሲሳይ |
| ዕድሜ፡ 66 | ዕድሜ፡ 58 | ዕድሜ፡ 36 | ዕድሜ፡ 30 |

## 8.2. በተፈጸመው ጥቃት የተገደሉ የአንድ ቤተሰብ አባላት ምስል፡

| | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| አቶ ጸጋዬ ጥላሁን መንገሻ | ወ/ሮ አበዘነች ገድሉ ተመናኘ | አቶ መለሰ ታፈሰ ወ/መስቀል |
| ዕድሜ፡ 68 | ዕድሜ፡ 70 | ዕድሜ፡ 50 |

| | |
|---|---|
|  |  |
| አቶ ንጉሴ ተክሌ መንገሻ | አቶ መስፍን ተክሌ መንገሻ |
| ዕድሜ፡ 35 | ዕድሜ21 ዕድሜ፡ 21 |

**8.3. በተፈጸመው ጥቃት የተገደሉ የአንድ ቤተሰብ አባላት ምስል፡**

| | | |
|---|---|---|
|  |  | **ፎቶ አልተገኘም** |
| ወ/ሮ መሰረት ጌቱ እሸቱ | አቶ ደሳለኝ አሰፋ ወ/ጻድቅ | ህጻን መስከረም ደሳለኝ አሰፋ |
| ዕድሜ፡ 35 | ዕድሜ፡ 40 | ዕድሜ፡ 2 ወር |

## 9. እገታ፡

በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ውስጥ ባሉ ቀበሌዎች በታጣቂዎች በተፈጸመ ጥቃት ሌላው የደረሰው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት አይነት እገታ ሲሆን ኢሰመጉ በአካባቢው በመገኘት ባደረገው ምርመራ መሰረት በእዚህ ጥቃት አንድ ግለሰብ በ24/03/2016 ዓ.ም ታግቶ ለ8 ቀን ያህል ከተያዘ በኋላ የተለቀቀ ሲሆን ኢሰመጉ በአካባቢዎች ከተጎጂዎች እና ከነዋሪዎች ጋር ባደረጋቸው ቃለመጠይቆች በተደጋጋሚ ጊዜ በታጠቁ ቡድኖች በአካባቢው እገታ እንደሚፈጸም እና ለታጋች ቤተሰቦች በመደወል የተመዘገቡና በባንኮችና በጸጥታ ኃይሎች ምርመራ ሊገኙ የሚችሉ የባንክ አካውንት በመንገር ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ መጠን እንዲያስገቡ እንደሚነገራቸውና ይህ ካልሆነ ግን የታገቱ ሰዎችን እንደሚገድሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ኢሰመጉ ይህንን የእገታ ድርጊት አስመልክቶ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎችና አውራ ጎዳና መንገዶች ላይ እና በአማራ ክልል ባሉ አንዳንድ አካባቢዎች በስፋት እየተፈጸመ ያለ የሰብዓዊ መብት ጥሰት መሆኑን በተደጋጋሚ ጊዜያት መግለጹ የሚታወቅ ሲሆን ነገር ግን ለእዚህ ድርጊት ተገቢው ትኩረት እና ህጋዊ ዘላቂ መፍትሄ ባለመሰጠቱ ምክንያት ድርጊቱ በተጠናከረ መልኩ እየቀጠለ መገኘቱ የሚያሳስበው መሆኑን መግለጽ ይወዳል፡፡

## 10. በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፡

ኢሰመጉ በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን፣ ጊዳሚ ወረዳ ልዩ ስሙ ቶኩማ መነሃሞ በተሰኘ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ አካል በሆነችው ጸሎት ቤት ህዳር 14 ቀን 2016 ዓ.ም በታጠቁ ቡድኖች ጥቃት መፈጸሙን የሚያሳዩ መረጃዎች የደረሱት ሲሆን ይህንንም አስመልክቶ መረጃ እና ማስረጃ እንዲቀርብለት በደብዳቤ ቁጥር ER3-N35-112-23 በቀን 11/04/2016 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ዋናው ጽ/ቤትን የጠየቀ ሲሆን ጽ/ቤቱ በደብዳቤ ቁጥር COO/5878/103/16 በቀን 15/04/2016 ዓ.ም በሰጠው መረጃ መሰረት ከሌሊቱ 8፡00 ሰዓት ለይ በጸሎት ላይ ከነበሩ 17 ሰዎች በታጠቁ ቡድኖች 9 የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ላይ የጅምላ ግድያ መፈጸሙን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ኢሰመጉ በአካባቢው በአካል የምርመራ ሰራተኞችን በማሰማራት የደረሰውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ምርመራ ለማከናወን በአካባቢው ባለው የጸጥታ ሁኔታ ምክንያት ማከናወን ባይቻልም ይህንን ድርጊት ኢሰመጉ ህዳር 28

ቀን 2016 ዓ.ም ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ ማሳወቁ  የሚታወስ ሲሆን አሁንም ከላይ እንደተገለጸው ከኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ዋናው ጽ/ቤት ያገኘነውን መረጃ እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ |
|---|---|---|
| 1 | ተሊላ ላሜሳ ታሲሳ | ወንድ |
| 2 | ቶሊና ላሜሳ ታሰሳ | ወንድ |
| 3 | ታምራት ላሜሳ ታሲሳ | ወንድ |
| 4 | ቃባና ቡልቻ ጉተማ | ወንድ |
| 5 | ጌታቸው ቤካታ ታደሳ | ወንድ |
| 6 | ሂካ አያና ያደሳ | ወንድ |
| 7 | ጅረኛ ድንጋታ ቴሶ | ወንድ |
| 8 | ሰለሞን ድንጋታ ቴሶ | ወንድ |
| 9 | ሲራጅ ዳኑ | ወንድ |

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ ከተቀመጡት መካከል ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 ያሉት ሰዎች የአንድ ቤተሰብ አባላት የሆኑ ወንድማማቾች ሲሆኑ ተራ ቁጥር 7 እና 8 ላይ የተጠቀሱትም እንዲሁ የአንድ ቤተሰብ አባል የሆኑ ወንድማማቾች ናቸው፡፡

## ተያያዥ የህግ ግዴታዎች፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 14 "ማንኛውም ሰው  ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው" ሲል ይደነግጋል። በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 15 ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ ከተደነገገው ውጪ ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይችል በግልፅ አመላክቷል፡፡ በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀጽ 16 ላይ ማንም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው ሲል ያስቀምጣል፡፡ የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች (ACHPR) አንቀጽ 4 ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት መብቱ ሊከበርለትና ሊጠበቅለት እንደሚገባና እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፈግ እንደማይችል ተመላክቷል። ዓለም አቀፍ  የሰብዓዊ  መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀጽ 3፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳንም (ICCPR) በአንቀጽ 6(1) እና  9(1) ላይ እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት እንዳለው ያረጋግጣል። ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል-ኪዳኑ (ICPR) የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2(1) እና 2(2) ይደነግጋል።

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀጽ 17 ማንኛውም ሰው ብቻውንም ሆነ ከሌሎች ጋር በመተባበር የንብረት ባለቤት የመሆን መብት እንዳለውና ማንም ሰው በዘፈቀደ ንብረቱን እንዲያጣ እንደማይደረግ ያረጋግጣል፡፡ የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች (ACHPR) በአንቀጽ 14 ላይ የንብረት ባለቤትነት መብት እንደሚረጋገጥ እና ሊጣስ የሚችለው ለህዝብ ፍላጎት ወይም ለህብረተሰቡ አጠቃላይ ጥቅም እና አግባብ ባላቸው ህጎች በተደነገገው መሰረት ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ይኸው ቻርተር በአንቀጽ 1 ላይ በዚህ ቻርተር ውስጥ የተካተቱት ሀገሮች በቻርተሩ ውስጥ የተካተቱትን መብቶች፣ ተግባሮች እና ነፃነቶች ተገንዝበው ተግባራዊ ለማድረግ የሕግ አውጭ

ወይም ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት በአንቀጽ 40 ሥር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ እንደሚከበርለት ይደነግጋል፡፡

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ አባል ሀገር ባትሆንም ሰዎችን አስገድዶ ከመሰወር ለመጠበቅ የወጣው ዓለም አቀፍ ሙሉ ስምምነት(International Convention for the Protection of All Persons from Enforced Disappearance) በአንቀጽ 1(1) ላይ ማንም ሰው ለአስገድዶ መሰወር ተጋላጭ መሆን እንደሌለበት በመደንገግ ይህንን ወንጀል የፈጸሙ አካላትን መንግስት በወንጀል ተጠያቂ እንዲያደርጋቸው ይደነግጋል፡፡

የፌደራል መንግስት በክልል ጣልቃ የሚገባበትን ስርዓት ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 359/2003 አንቀጽ 7-11 በጠቀመጠው መሰረት የፌደራል መንግስት በክልሎች ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሲፈጸሙ እና የክልሉ መንግስት ይህንን መቆጣጠር ካልቻለ የፌደራል መንግስት ጣልቃ እንዲገባ፣ አጣሪ ቡድን እንዲልክ እና መመሪያን ለክልሎች እንዲሰጥ ሀላፊነት ይጥላል፡፡

## የኢሰመጉ ጥሪ፡

- የፌደራል መንግስት እና የኦሮሚያ ክልል መንግስት በክልሉ በተጋጋሚ በታጣቂ ቡድኖች ማንነትን መሰረት አድርጎ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በአስቸኳይ እንዲያስቆሙ፣
- የፌደራል እና የኦሮሚያ ክልል መንግስት የህዝቡን ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት እያለባቸው ይህንን በቸልተኝነት ሳያደርጉ የቀሩ የመንግስት አካላትን በህግ እንዲጠይቁ፣
- መንግስት በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ የተለያዩ ቀበሌዎች ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የፈጸሙ አካላትን በህግ እንዲጠይቅ፣
- በምስራቅ አርሲ ዞን ሽርካ ወረዳ ውስጥ ባሉ ቀበሌዎች ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ለተፈጸመባቸው ሰዎች ተገቢው ካሳ እንዲሰጥ፣
- በኦሮሚያ ክልል ህዳር 14 ቀን 2016 ዓ.ም ቄለም ወለጋ ዞን፣ ጊዳሚ ወረዳ በኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ አባላት ላይ ግድያ የፈጸሙ ሰዎችን የክልሉ መንግስት በህግ ተጠያቂ እንዲያደርግ፣
- በኦሮሚያ ክልል በተደጋጋሚ በታጣቂዎች ለሚፈጸሙ ጥቃቶች የክልሉ እንዲሁም የፌደራል መንግስት የጸጥታ አካላት ጥቃቶች ሳይደርሱ ቀድሞ የመከላከል ስራን ጥቃቶችም በሚደርሱ ጊዜ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ስራን ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩበትና መሰል ጥቃቶች እንዳይደርሱ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት

  ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 80001፣ ኢ.-ሜል፡- national.parliament@telecom.net.et

  ፋክስ ፡- (+251) 011 155-0400፣የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 124-1000፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

  ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 20122/1000፣ ኢ.-ሜል ፡- kumashih@gmail.com

  ፋክስ ፡- (+251) 011 124-1208/011 124-2308፣

  የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 122-3322፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት:-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 23698፣ ፋክስ ፡- (+251) 011 551- 8656፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-8186፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ፡-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡-1031፣ ፋክስ፡- (+251) 011 122-6292፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 124-1155፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር

  ስልክ ቁጥር +251 115541868 ፋክስ +25115517775

  ኢሜይል MOJMO@ETHIONET.ET

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሰላም ሚኒስቴር

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 5608፣ ኢ.-ሜል፡- mofatr1@yahoo.com

  ፋክስ፡-(+251)011 551-1200፣ የስልክ ቁጥር፡-(+251) 011 515-3204፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 2459፣ ኢ-ሜል፡ ombudsmaneth@ethionet.et

ፋክስ፡- (+251) 011 553-2073፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 543-336፣

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን:

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1165፣ ኢ-ሜ፡ hrcom@ethionet.et፣

ፋክስ፡ (+251) 011 550-4125፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 550-4031፣

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀነራል ጽ/ቤት:

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 199፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-2744፣

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለሱማሌ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔጽ/ቤት:

ፖ.ሳ.ቁጥር 392፣ ፋክስ፡- (+251) 25 775-3429፣

የስልክ ቁጥር፡ (+251) 257 75 34 29

ጅግጅጋ፣ ኢትዮጵያ

- ለሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 588 ፋክስ፡- (+251) 025 775-2325፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 775-4038 / 025 775-3241 ጂግጂጋ፣ ኢትዮጵያ

- ለኦሮሚያ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769፣ ኢ-ሜል፡- oromiawiev@ethionet.et

ፋክስ፡- (+251) 011 551-3642 / (+251) 011 551-9633፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 552-4247፣

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769 ፋክስ፡- (+251) 011 552-4247

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 555-0455

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1324፣ ፋክስ፡- (+251) 058 220-2511፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-2659

ባሕርዳር፣ ኢትዮጵያ

- ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 312 ፋክስ፡- (+251) 058 220-1068፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-0924 / 058 220-0499

ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ

- ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

ፖ.ሳ.ቁጥር፡-

የስልክ ቁጥር፡-

ቦንጋ፣ ኢትዮጵያ

- ለሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዘዳነት ጽ/ቤት

ኢ-ሜይል አድራሻ፡-sidaamapoffice@gmail.com

የስልክ ቁጥር፡-

ሀዋሳ፣ ኢትዮጵያ

- ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1546፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 221-4778/ 046 220-5848፣ ሐዋሳ፣ ኢትዮጵያ

- ለደ/ብ/ብ/ህ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 18 ፋክስ፡- (+251) 046 220-1641፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 220-9166

ሃዋሳ፣ ኢትዮጵያ

- ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 44፣ ፋክስ፡- (+251) 057 775-0814፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 055 7775-0109፣

  አሶሳ፣ ኢትዮጵያ

- ለትግራይ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 291፣

  ፋክስ፡- (+251) 034 441-6564፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 034 441-6563፣

  መቀሌ፣ ኢትዮጵያ

- ለጋምቤላ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 25፣ ፋክስ:- (+251) 046 220-2408፣

  ጋምቤላ፣ ጋምቤላ

- ለጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 025

  የስልክ ቁጥር:- (+251) 047 551-154

  ጋምቤላ፣ ኢትዮጵያ

- ለሐረሪ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 952 ፋክስ፡- (+251) 025 666-2530፣

  የስልክ ቁጥር:- (+251) 025 666-1723 / 025 666-1746

  ሐረር፣ ኢትዮጵያ

- ለሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 272 ፋክስ፡- (+251) 025 666-0666፣

  የስልክ ቁጥር:- (+251) 025 666-1799

  ሐረር፣ ኢትዮጵያ

- ለአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት

  ስልክ ቁጥር (+251) 0336660056

ሰመራ ኢትዮጵያ

- ለድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት

  የስልክ ቁጥር፡ (+251) 025 11 11 358

  ፋክስ፡ (+251) 025 11 19 805

- ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት

  ስልክ ቁጥር (+251) 0118591363